# <u>ግልፅነት ወይስ ብልጣብልጥነት ጠቃሚው!</u>

ዘነበ በቀለ

ዘመን ሩዋጭ ነው። የራሱን ፍጥነት ወሳኙ አራሱው ጊዜ ነው። ብቻ “ጊዜ አግኝቶ አለሁልህ ማለትን ለማያውቅ ጊዜው ሲያልፍበት አለሁልህ የሚለው አያገኝም” ነውና ነገሩ ጊዜው ሲበን እየረጋገጠ የሚያልፋቸውን ተመልክቶ ከመሳቅ ይልቅ ነግ በኔ ብሎ ቢተባበር የሰው ልጅ በተሰጠው የጊዜ ገደብ የላቀ ነገር መስራት በቻለ ነበር። እኛ ኢትዮጵያውያን ከሁለት ሺው ምዕት ዓመታችን ጋር ትናንሿም የሰው ልጆች ዕድሜ ኩት ኩት ማለቷን እያየን “የፋሲካው በግ በዳግማይ ትንሳኤው ይሰቃል” እንዳሉት መንከትከታችን አልቀረም። በእርግጥ ጊዜን ማስቀም አይቻልም። ቢቻል ኖሮ የኢትዮጵያ ህዝብ ባግባብ የኖረባቸውን ብቻ ቆጥሮ የቀሩትን በማጠፍም ዘላለም ልጅ ሆኖ በቆየ ነበር። ከሃምሳ ዓመት በሁዋላ በምድር ላይ የሰው ልጆች ከ6.5 ቢሊዮን ወደ 9.1 ቢሊዮን ከፍ ይላሉ ተብሏል። ያን ጊዜ እንደልብ የሚያፍሱት ምድራዊ ሀብት ሲቀንስ ተስገብጋቢዎች ዕጣ ክፍላቸው ምን ይሆን ይሆን? ወይስ በለመዱት እብሪታቸው ሊቀጥሉ ይሆን? ይህ የኔና የኔ ዕድሜ ክልል ያሉ ሁሉ ሰዎች ሃሳብና ጭንቀት ነው። ለወቅቱ ደራሽ ትውልድ ደግሞ ጭንቀቱን በአግባብ ሊረዳው ይገባል። የእኔ ትውልድ መጪው ዘመን ከመድረሱ በፊት ተዘጋጅቶ መጠበቅ ማስፈለጉን በማመን በህዝባዊ መብቶች መከበርን ባንድነትና በፍቅር የመኖርን ጠቃሚነት ከማይፈልጉ ጋር ሁሉ ሲፋለም ኖሯል። አሁንም ፍልሚያውን ይቀጥላል።

የሰማዩ ላይ መመንጠቅ፤ የምድር ውስጡ ስርገት ሁሉም ከተፈጥሮ ቁጣ የሚድኑ ሆነው አልተስተዋሉም። አውሎ ነፋሱን ጎርፉን ሰደድ አሳቱን የተቆጣጠረ ስልጣኔ እስካሁን ባለመታየቱም ሃያል የሚባል የሰው ጥበብ “አንድነትና ህብረት” ፈጥሮ በመተሳሰብ መጓዙ ብቻ እንደሆነ ተመስክሯል። ለውጡን ተከትሎ ፍጥነቱን ጨምሮ የበነነ ግለሰብ እራሱን ለማትረፍ የሚችልበት መንገድ አለ ብሎ ባስተማማኝ መናገር ያስቸግራል። ዐቅም አለኝ ብሎ ሮጦ ካደጋ ለማምለጥ ከሚሞክረው ሰው በፅናት እቤቱ የተቀመጠው ሰው ከአደጋው እንደሚተርፍ ሲታይ በአንፃሩም በአይሮፕላን ተሰቅሎ የሚሄደው ሰው ከሚደርስበት አደጋ ይበልጥ መንደሩ ቁጭ ብሎ ፀሃይ በሚሞቀው ላይ የተከሰከሰው አይሮፕላን ጉዳት ሲደርስበት ተስተውሏል። ስለዚህም ተሽቀዳዳሚው ቢበዛም ካሰበው ደራሹ ጥቂት ነውና እርምጃን ማስተካከሉ ተገቢ ነው። የተኚው መበርከት የአላሚውን ቁጥር ከፍ ሊያደርገው አይችልም። የሚያልሙትም አይነት ይለያያቸዋል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ተደጋግፎና ተከባብሮ መጓዝ ሲገባው ሌላውን ገፍትሮ ጥሎ ማለፍ በሌሎች ላይ የበላይነትን ለማሳየት ልዩ ልዩ ማታለያ ዘዴዎችን መጠቀም እንደ አራዳነትና እንደ ዘመናዊነት የሚቆጠር ከሆነ ችግር አለ። መዘዙ ዐቅም የሌለው ይሙት! የሚል መደመደሚያ ላይ አያደርስንም። ከዚያ የከፋ ነው የሚሆነው። መማር መመራመር የግል ሀይልን ሀብትንና ፈላጭ ቆራጭነትን ያስገኝልኛል፤ ለተወዳጅና ለአሳሳች ዲስኩር ብቃትን ይፈጥርልኛል ብሎ ፊደል የቆጠረው ሁሉ በእርግጥም እንደገና ወደየኔታ ተመልሶ እራሱን ማስመርመር የሚገባው በመሆኑ ትምህርት ቤቶችን እንዳያጣብብ ያሰጋል። የኔታ ያልተናገሩት ያልገለፁት ነገር ይኖራል ማለት የሚቻል አይሆንም። በዶር. ሀይሉ አርአያ “ያገር ፍቅር ልክፍት” ግጥም ውስጥ መንፈሱ ተንፀባርቋል።

የኔታ ለማንም አዳልተው እንደማይናገሩ ሁሉ ማንንም ጠልተው ፍቅራቸውን እንደማይነፍጉ ሀቅ ነው። ማንም ግን እሳቸው ዘንድ የደረሰ ይህንን የህብረትና ያገር መውደድ መንፈስ ሳይገነዘብ ይወጣል የሚል ግምትም የለኝም። ዐለም በግለኝነት ስሜት ልትወጠር ወይም ልትገዛ ይቻላታል ብሎ የሚያምን ተማርኩ ባይ ካለ ችግሩ ከየኔታ ሳይሆን ከራሱ ድክመት ነው። ሀይል እውቀት ጥበብ ፍቅር ሁሉም የሚገኘው በህብረት ነው። ህብረትን አንድነትን የሀገር ፍቅርን ያንኳሰሰ ትምህርት ግን ድንቁርና ነው ሊሆን የሚችለው። ተማሪው ዕውቀትን የሚያገኘው ካስተማሪው ቢሆንም አስተማሪውም ጥበብን የሚቀሰመው ከህዝብ የወል ፍላጎት ነውና ዕውቀት ሁሉ ተወራራሽ ነው። ከህዝብ የጋራ ስሜትና ፍላጎት ውጭ በዓለም ላይ ምንም ነገር ዘላቂነት የሌለው መሆኑን ማመን ያስፈልጋል። የህዝብ ፍላጎትና ዐቅም ደግሞ ከአእምሮ ዕድገት ጋር ስለተቀናጀ ነው ስርአተ ማህበራት የመለዋወጥ ዕጣ የገጠማቸው። ያ ባይሆን ኖሮ አምራችነት በአዳኝነት እግር ባልተተካ ነበር። ህዝባዊ ባህልም ባልገዘፈ ነበር።

ጀበናንና ስኒን ነጣጥሎ የሚስል ሰዓሊ ምናልባት ሊል የፈለገውን ለማለት የሚያስችለው መንገድ መርጧል አልልም። ምክንያቱም ጀበናና ስኒ የተዋሃደና የተወሰነ  ተግባር የሚፈፅሙ በመሆናቸው በተናጠል እንዲቀርቡ ማድረግ ተግባራቸውንም ሆነ ውጤታቸውን ሰንካላ ያደርገዋልና ነው። የእስክስታና የረገዳ ጭፈራ፤ ዘፈንና መዝሙር የህብረ ድምፅ ዜማ ህዝባዊነትን ህብረትን አንድነትን ፍቅርን ባይላበሱ ኖሮ በነጠላነት ወይም በእንጉርጉሮ ላይ ተወስነው የግል ሙዚቃዎች ሆነው በቀሩ ነበር።
ስለዚህም ነው ሁልጊዜ ህዝባዊነት በጋራ ልማት በጋራ ብልፅግና ቀዳሚውን ስፍራ መያዝ የሚገባው። ግለኝነት ነጠላ በመሆኑ ቢያደምቅም አያሞቅም። ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያ ሀገራችን ናት ስንል እኛ በዚያች ምድር ላይ የተፈጠርን ሁሉ፤ በህዝቧ ቀንጆ ባህሎች የተቀረፅን፤ በቋንቋዎቿ የተዋብን፤ ለህልውናዋ የምንቆረቆር፤ ኢትዮጵያውያን ነን ማለታችን ነው። ከሀገራችን የበለጠ እራሳችንን እማንወድ፤ ከህዝባችን ታሪክ ውጭ ታሪክ የሌለን፤ ለዕድገቷ ለብልፅግናዋ ለአንድነቷ ሲባል ለህይወታችን የማንሳሳ እኛ ብዙሃን ኢትዮጵያውያን ነን ማለታችን ነው። ለአንድነትዋ ለታሪኳ ለብልፅግናዋ ለዲሞክራሲ አስተዳደሯ ሲባል በየትኛውም አቅጣጫ ግለሰቦች ህይወታቸውን ለግሰው የወል ክብርን አንግሰዋል። ህዝቧ ኩሩ ዜጋ ሆኖ እንዲኖር አድርገውታል። በመሆኑም እኛ ኢትዮጵያውያን ነን ስንል በርካታ ጀግኖች የአሏት ሀገረ ኢትዮጵያ መሆኗን መመስከራችን ነው። ስለዚህም እንደምን ተደርጎ ይህ የአንድነት የህብረትና የጋራ የሆነ ታሪክ፤ በራስ አምላኪዎችና በስልጣን አምሮታም ቡድኖች ሊጨናገፍ ይችላል?

ህዝብ ግለሰብ መሪዎችን የሚመርጠው በሀቀኝነታቸውና በታማኝነታቸው ለይቶ አውቆ ተግባሩን እንዲያከናውኑለት ደሞዝ ከፍሎ ያሳድራቸዋል እንጂ! የየራሳቸውን ሹማባሽ እየሾሙና እየሸለሙ የራሱን ገንዘብ ወጭ አድርገው የግል ጠባቂ ወታደርን ቀጥረው እራሱን እንዲያፍኑትና እንዲአሰቃዩት ፍላጎት የለውም። ህዝብ ደጋፊዬ አለኝታዬ አጋዤ ብሎ እሚለው ወሬ አወቅን ተማርን ተመራመርን ብለው እንዳሻቸው የሚዝናኑበትና የሚዘባነኑበትን ሳይሆን በችግሩ ከጎኑ ቆመው ሃቁን ለማውጣት በጥቅማጥቅም ሳይታለሉ የሚሞግቱለትን ነው። ለዚህ ያጫቸው ሁሉ የተሰጣቸውን ተግባር ስተው ሲራመዱ በሚረጩት ጭቃ ከመበከሉ በፊት አቁም የማለት ሙሉ ስላጣን ያለው ህዝብ ነው። አሁንም በቅንጅት መሪዎች መካከል የሚታየው ቲያትር ባለመብቱ የኢትዮጵያ ህዝብ ጣልቃ መግባት እንደሚኖርበት የታወቀ ነው። የሰሞኑ ግርግር የህዝብን ፍርድ ይጠይቃል። ጉዳዩ የሱው ነውና ፍርድ መስጠትም አይገደውም።

ለመሆኑ ትያትሩ ከየት ተጀመረ? ተዋንያኖቹስ? የድርሰቱ አቅራቢስ ማነው?

ትያትሩ የተዋሃደ የአሰራር ስልት የተከተለ እንደሆነ ከፖለቲካው አመራር ይልቅ በዚህ ድራማ ላይ ይንፀባረቃል። የቅንጅት መሪዎች በእስር ላይ በነበሩበት ጊዜ በውስጣቸው የነበረውን ጉዳይ ከራሳቸው በላይ የሚያውቀው ባይኖርም በእስር ቤቱ ውስጥ ሲፃፍ ሲፈበረክና ለመድረክ ሲቀነባበር መሰንበቱን አሁን ከእስር ከወጡ በሁዋላ በምናየው ኮሜዲ መገንዘብ እንችላለን። ድርሰቱ “ኢንጂነር ሀይሉ” ደራሲው ዶር. ብርሃኑ ነጋ አቀነባባሪ “አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ” የመድረክ መብራት “አቶ ብርሃነ መዋ” ገፀ ባህርያት “ሻለቃ ዮሴፍ ያዘው” አቶ “ሰሎሞን በቀለ” “ዶር.ታዬ ወልደስምያት” ስፖንሰር የዐለም አቀፍ አመራር ሰጭ አካል ተቀማጭነቱ በውጭ ሀገር የሆነ፤ ተዋንያን “ወይዘሮ ብርቱካን ሚዴቅሳ” “ዶር. ሀይሉ አርአያ” “አቶ ብሩክ ዳዊት” “ኢንጂነር ግዛቸው ሽፈራው” ታዳሚዎች የዐለም አቀፍ መዋቅር ቻፕተር ተጠሪዎች። መድረክ አዘጋጅ “አቶ አክሎግ እና ተባባሪዎቹ” እና ሌሎችም በአስተናጋጅነት የተካፈሉበት ትያትር ከቃሊቲ ተዘጋጅቶ ሲመጣ በዋሺንግተን በተደረገው የመጀመሪያ ትርኢት ላይ ደራሲው ዶር ብርሃኑ ስለድርሰታቸው ይዘትና አላማ ማብራሪያ ሰጥተውበታል። ኮሌክቲቭ ሊደርሺፕ የአቶ አንዳርጋቸው ፈጠራ ብቻ ሳይሆን የነ ኢንጀኔር ግዛቸው ምስክርነትንም ያገኘ በመሆኑ በትያትሩ ፅንሰ ሃሳብ ላይና በአፈፃፀሙ ላይ ጊዜ የወሰደ ቅንብር መሆኑ በግልፅ ይታያል። ይበል ባይሰኝም ባቀራረብ ስልቱ አድናቆትና ግርምት የሚቸረው ነው። የትያትሩ መልዕክት ያው እንደ ርዕሱ ኢንጂነር ሀይሉ ሻውል መወገዝ ያለባቸው መሆኑን ነው የሚያበስረው።

በመሰረቱ ለህዝብ ቅርብ ሆኖ ለህዝብ መብት የተሟገተ ሁሉ ሊወቀስና ሊንጓጠጥ አይገባውም ነበር። ለህዝብ መብት ሲል የራሱን የግል ዕድገት የገታ መስዋዕት ያደረገ ሁሉ ሊከበር እንጂ ሊሰደብ

አያበቃውም። ግን ትያትሩ እራሱ የወጣው ከዚሁ አካል በመሆኑ “ባለቤቱ የናቀውን አሞሌ ባለ ዕዳ አይቀበለውም” ብለን አናልፈውም። አሞሌነቱንና ድንጋይነቱን እንመረምራለን። ትያትሩንም ከመነሻው ጀምሮ ልንገመግመው እንገደዳለን። የትያትሩ መልእክት ይማርካል ተብሎ ሳይሆን የተዋናዩ ስብጥርና ችሎታ አይን ይስባል ተብሎ የተገመተ ይመስላል። በርቀት የሚመለከተው ተራው ህዝብ ደግሞ ጥያቄውን ከማቅረብ አልተቆጠበም። ለመሆኑ ይህ ትያትር ለኢትዮጵያ ፖለቲካም ሆነ ለኢትዮጵያ ጎስቋላ ህዝብ የሚያተርፈው ነገር ምንድነው?

ዘመናዊዎቹ የቀይጥ ኤኮኖሚ አቀንቃኞችና የግል ብልፅግና አምሮታሞች ጥቅማቸውን ለማስከበር የማይፈነቅሉት ድንጋይ አለ ብሎ ማመን አይቻልም። በታጋዩ ላይ ሁሉ የሰላ ትችትና ጥላቻ ሲያሳድሩና ድንጋይ ሊያስወረውሩ ሲከጅላቸው ማየት አዲስ ነገር ሊሆንም አይገባም። ብቻ ኢትዮጵያ ወደ ልማት መሸጋገር የምትችለው የህዝብን ፍላጎትና መብት ማክበር ሲቻል መሆኑን እስካሁን ያለተገለፀላቸው ሰዎች መኖራቸው ሊያስገርም ይችል ይሆናል። መወነጃጀሉ ቀርቶ ለህገር ጠቃሚ ስራ ለመስራት ከተፈለገ ያንድ ወጥ የፖለቲካ አሸናፊነትን ከጭንቅላት ማስወገድ በተገባ ነበር። የግለሰብ ምኞትን በህዝባዊ ፍቅር መለወጥ በተገባ ነበር። ከዚህ ውጭ የሚደረግ ትያትር ያው! በኮሜዲነቱ ታይቶ የሚያልፍ ከመሆን አይዘልም።

ዛሬ ሀገራችን የምትፈልገው አንድ ጠንካራ ቅንጅትን ብቻ አይደለም። ከኢህአፓ ጋር በፍራቻ በሩቅ ከመሸሽ ተቆጥቦ በቅርብ አብሮ መስራት ያስፈልጋል። ኢህአፓ በጣም የዳበረ የትግል ስልት ያለው ድርጅት መሆኑን ለመረዳት ብዙ መጓዝ አያስፈልግም። እንዴት አድርጎ ከደርግ ጠላትነት ተርፎ እስካሁን ለመቆየት ቻለ? አባላቱን ለትግል ለማሰለፍ ምን ያህል ጊዜ ፈጀበት? እንዴት አድርጎ በወያኔ ደባ ሳይጠለፍ እራሱን ጠብቆ በመቆየት የነታምራት ላይኔን ያስከሬን ስብሰባ ድራማ በማጋለጥ የራሱን ክሎኖች ለማሳፈር በቃ? እንዴት አድርጎ ዛሬም ጠፉ ያሉት ጠላቶቹ አላሰራ አለን ብለው እስከመናገር ደረሱ? ብሎ መጠየቅ መልሱን ሊያስገኝ ይችላል። የድርጅቱን የትግል ልምድና ብቃት ለመገንዘብ አይንን መጨፈን ተራ ጥላቻን እንጂ! ለህገር ለወገን አሳቢነትን አይገልጥም። ደክመዋል ጠፍተዋል ብሎ ከማሰላት እምነታቸውን በነፃነት እንዲያራምዱ የኢሰፓን አባላት በወዳጅነት ዓይን መመልከት ያሻል፤ የኢዴዩን አባላት፤ የመኤሶንን አባላት ማክበር ያስፈልጋል። ኢህአዴግም በወያኔ የበላይነት የግል ጥቅሜን አስከብራለሁ ብሎ ከመጃጃል ርቆ እንደ አንድ ድርጅት መሆኑ ታምኖለት መብቱ ተጠብቆለት በእኩልነት መንቀሳቀስ ይኖርበታል። ከሌሎችም ጋር ሁሉ ተቀራርቦ መስራት የሚያስፈልገው ስለዚህ ነው።

እምነትን በሆድ ደብቆ ላይ ላዩን አጭበርባሪ የሆነ ቋንቋ እየተጠቀሙ መዝለቅ አራዳነትን አይመሰክርም። ይልቁንስ! የሚያምኑበትን በግልፅ አሳውቆ በአሰራር ስልቱ ላይ መደራደር ይበልጥ ዲሞክራሲን ያጎለብታል እንጂ አያኮስምንም። ይህ ሁሉ የሚሆነው ግን ቅንነትን ሀገር መውደድን ህዝባዊ ፍቅርን ስንላበስ ብቻ ነው። የኔ ብቻ ፖለቲካ፤ ረግጬ ልውጣው ፖለቲካ፤ ውጤቱ ምን እንደሆነ አይተነዋል። እስካሁንም አልሰራ ወደፊትም የሚሰራ አይደለም። የሚሰራ ቢሆን መስራት የሚችለው በዛሬው የቀይጥ ኤኮኖሚ አዋጅን ተመርኩዞ ሳይሆን በሶሻሊዝሙ ግዳጅ ጊዜ በሆነ ነበር። በተናጠል በሚሄዱ ሃይሎች ጊዜያዊ ጉንፋን ህዝብ እያነጠሰ እንዲቀጥል መፈቀድ የለበትም። ይህ አይነቱ ድርጊት ለህገር ልማት ጠቃሚና ገንቢ ልምድ ነው አይባልም። ዛሬ ጠቡ በዲሞክራሲ ጉዳይ ላይ ብቻ ሳይሆን በነፃነት ጥያቄ ላይ ነው። በቀይጥ ኤኮኖሚ ሰበብ ሀገር በቅኝ ገዥዎች እጅ እየወደቀች ነው። ዲሞክራሲ በስሙ እንጂ በግብሩ ሰው ሲያጠግብ የታየበት ስፍራ ባለመኖሩ ባልታየ ፍልስፍና ላይ ጊዜ ማጥፋቱ ፋይዳቢስ ነው። ያም ቢሆን የሀገር ህልውና አደጋ ላይ በወደቀበት ሰዓት አይደለም። የኛው ጉዳይ መሆን የሚገባው ለሀገር ህልውና መጠበቅ በፅናት መቆም ነው። የዲሞክራሲው ጥያቄ ሊፈታ የሚችለውም የህልውናችን ጥያቄ አስተማማኝ ሲሆን ብቻ መሆኑ ግንዛቤ ሊያገኝ ይገባዋል።

ኢትዮጵያ በነፃነቷ ኮርታ ለዘለዓለም ትኖራለች!